# ለመላው ኢትዮጵያዊ ጥሪና መልዕክት

በአሁኑ ወቅት የወያኔ አገዛዝ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወደ ውደቀቱ እያመራ ነው ፡፡ ከባድ ቀውስ ውስጥ ገብቷል ፡፡ ሕዝብ በደሉን አልቀበል በሚል የወያኔን መወገድ ለማረጋገጥ ፈልጓል፡፡ የአገዛዙን ቀውስ--በመለስ ሞተ ታጀበ አልታጀበ -- ለመሰረታዊ ለውጥ ለመጠቀም ከተነሳን ከወያኔ አገዛዝ ጋር መሞዳሞድ ከቶም የሚታሰብ አይሆንም ፡፡

ይድረስ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ

የወያኔ አገዛዝ ወደ ውድመቱ እያመራ ነውና ሕዝባዊ ትብብር ግዳጅ ሆኗል፡፡ ስለዚህም የተጀመረውን ሕዝባዊ ተቃውሞ መደገፍና ማጀብ. ግዴታችሁ ነው፡፡ በዝምታ ማየት በራስ ላይ ጥፋትን መጋበዝ ነው ፡፡ አንዱ ሲነሳ ሌላው ከደገፈው ውጤቱ አመርቂ ይሆናል፡፡ የየካቲት 66 አብዮት ተመክሮ ደግሞ ይህ ነው ፡፡ አብዮቱ ወደፊት የገፋው ከልዩ ልዩ የህብረት ሰቡ ክፍሎች የመጡ ዜጎች የየራሳቸውን ጥያቄ ቢያነሱም በጋራ ግን የስርዓቱን ለውጥ በመጠየቃቸው ነው ፡፡ ይህ የትግል ህብረት ደግሞ ለስርዓቱ ውድቀትና ለጥገና ሙከራዎች መክሸፍ ምክንያት ሆኗል፡፡ ዛሬ ግን ይህ ሁኔታ ተሟልቶ እየታየ አይደለም፡፡ ያኔም ቢሆን ስርዓቱን በጥገና ለውጥና በመሞዳሞድ ዕድሜ ሊሰጡ የፈለጉ ፤ ለእንዳልካቸውመንግስት ጊዜ እንስጠው ያሉም ነበሩ፡፡ ቆይተው ለደርግም ጊዜ እንስጠው ብለዋል፡፡ በ1983 ም ለነ መለስ ጊዜ እንስጥ በሚል፤ ዱላ ተዉ ባይ ዕርቅ ሰባኪዎች ጮኸው ተረባርበው የሕዝብን ትግል ያዳከሙ ነበሩ ፡፡ ይህ ሁሉ በቂ ተመክሮ ነው፡፡ ዛሬ ሊደገም አይገባውም ፡፡ በዚህ የቀውስ ጊዜ ተመልሰው ከወያኔ እንተባባር በሚል የሚሰብኩትን አብዮት አጥፊዎች ጆሮ ሕዝብ ሊሰጣቸው አይገባም፡፡ በጋራ በወያኔ አገዛዝ ላይ መነሳትና መለስን ብቻ ሳይሆን አገዛዙን ሁሉ ማውደም ሀገራዊ ግዳጅ ነው፡፡

ይድረስ ለጦር ሀይሎች አባላት በሞላ

የአገዛዙ ህይወት ጠባቂ እናንት ናችሁና አቅዋማችሁን በመቀየር ከሕዝብ ጎን መሰለፍ ግዴታችሁ ነው ፡፡ የመለስ አገዛዝ በጥቅማ ጥቅሞች ሊደልላችሁና ለፀረ ሕዝብ ግቡ ሊጠቀምባችሁ ሲጥር ዓመታት አልፈዋል፡፡ በናንተና በሰፊው ሕዝብ መሀል ቂምና ቅራኔ አለ ፡፡ ደም በብዛት ፈሷል--እናንተም የሕዝብ ጦር መሆኑ ተስኗችሁ የአምባገነን ቡድን መሳሪያናመጠቀሚያ ሆናችሁ አላችሁ ፡፡ በዘረኝነት መረዙም የበካለችሁ ጥቂቶች አይደላችሁም፡፡ ኮር፤ አግአዚ፤ ፌዴራል ወዘተ ሁላችሁም በሕዝብ ጠላትነት ተፈርጃችኋልና ያ ቀን ሲመጣ ይዞታችሁ ከቶም ጥሩ አይሆንም፡፡ ዛሬ የአገዛዙ ቀውሰ ተባብሶ ወደ መቃብሩ

ጉዞው እየተፋጠነ ነው ። ዛሬም ለወያኔ ታዛዥ ሆናችሁ ለመገኘት ከመረጣችሁ የሚመጣው የአመፅ ጎርፍ ጠርጎ ጠራርጎ የሚወስዳችሁ ይሆናል። ሕዝብ ድልን ሲቀዳጅ ይፋረዳችኋል ። ይህን ሀቅ ተረድታችሁ ሰልፋቹን ከሕዝብ ጎን ታደርጉ ዘንድ በድግግም ጠርተናችኋል። ጆሮ ያለው ይስማነው መልዕክቱ ። ይህ መልዕክት በወያኔና ተለጣፊ መዋቅሮቹ ያሉትን ካድሬዎች ና በባዕድ ሀገሮችም ያሉትን የወያኔ አባላትና ደጋፊዎች ሁሉ ይመለከታል ።

ይድረስ ለኢትዮጵያ ላባደሮች፤ አርሶ አደሮች፤ ተማሪዎችና አስተማሪዎች በሞላ፤

በህብረተሰባችን ያላችሁ ሚና ክብደቱ ከፍተኛ ነው ። በተማሪ፤ አስተማሪና የቢሮ ሰራተኞች የተደገፈ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ትግል ለድል የሚበቃ ይሆናል። ኢትዮጵያ ደግሞ አብዛኛው ሕዝቧ ላባደርና ሰርቶ አደር ነው። እናንተ ከዚህ ቀደም እንዳደረጋችሁት አብዮት ማምጣት ትችላላችሁ ። ከእናንተ ውጪም አብዮት ሰሪ ፤ ሕዝባዊ ለውጥ አምጪ ሀይል የለም ። ለዚህም ነው መነሳተ ማመፅ የሚገባችሁ ። ሊመሩ የሚገባቸው ድርጅቶች ከደከሙ·እናንተ በራስ አነሳሽነት ሰብሰበ ብላቸሁ ለመታገል መጣር አለባቸሁ። ሀገራዊ ግዴታ ነው። ሌላ አማራጭም የለም ። የሚያታገሉ መሰረታዊ የመብት፤ የዴሞክራሲ፤ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ጥያቄዎቻችሁ አያሌ ናቸው ። መሬት ለአራሹ፤ የሀገራችን ለም መሬት ለባዕዳን አይሸጥ ፤ አንፈላቀል፤ ገዳሞቻችን መስጊዶቻችን ተደፈሩ ፤ የሀገራችን መሬት ለባዕድ ተሰጠ ፤ የኑሮ ወድነት አደባየን፤ ዘረኝነት ጎዳን ወዘተ በሚሉ አበይት ጥያቄዎችና ጉዳዮች ዙሪያ ተቃውሞን ማድረግ ይቻላል። ተማሪዎችና አስተማሪዎችም ሀገራዊም የራሳቸውም ጥያቄዎች አሏችሁ። ታክሲ ነጂዎች፤ የቢሮ ሰራተኞች ከየካቲት 66 በባሰ አስከፊ ሁኔታ ላይ ናችሁ ።በተናጠል ተቃውሞውም የሚያዋጣ አልሆነም ። ለዚህም ነው በጋራ ተቃዋሞ ወያኔን ማራደ ማንቀጥቀጥ የሚገባችሁ። ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ሲሰለፉ ከጎናቸው መገኘት አለባችሁ ። የስራ ማቆም አድማ መሳሪያችሁን ተጠቀሙበት። ከሀዲን ከመሀል መመንጠርን በተመለከተ ደግሞ ትምህርትም የሚያስፈልጋችሁ አይደላችሁም ። መሰረታዊ ለወጥ ማለትወያኔን በወያኔ መተካት አለመሆኑን ታውቃላችሁና ለአብዮታዊ ለውጥም ማለትም ለወያኔ አገዛዝ መውደም መታገል አለባችሁ ። ለነፃነታችሁና ለሀገራችሁ ሉዓላዊነት ከናንተ ሌላ ታጋይ የለም ። ለዚህም ነው ለመስዋትነት ዝግጁ ሆናችሁ ለወሳኙ ትግል እንነሳ የሚል ጥሪያችን የሚቀርብላቸሁ ።

ተቃዋሚዎች ነን ለምትሉ ሁሉ ጥሪ

መሳቂያ መሳለቂያ ከመሆን ለመራቅ እንጣር ። መተባበር መቀናጀት የምትችሉ ተባበሩ ። የሆነ ያልሆነ አቋምን በመያዝ ሕዝብን አታሳፍሩ ፤ መሳቂያ አትሁኑ ። ፀረ ወያኔንም ትግል በጥገና ለውጥ ሰበካ አታደፍርሱት። መለስ ሞተ አልሞተ በሚለው ዙሪያ ያሳያችሁትአሳዛኝ፤ አስፈሪና አስገማች ነበር። ራዕይ ያላቸው ወያኔዎች አሉና ከነሱ እናብር ያላችሁትም የሰማውን ዜጋ ሁሉ አሳዝኖታል። መቶ መቶ ሀምሳ ሆኖ በአሜሪካ መሰለፉ የትግል አልፋና ኦሜጋ አይደለም። ዋናው ትግል በሀገር ቤት ነው። በዚህ መድረክ አለና ካላላችሁ ርባና ቢስ ናችሁ ። ካለፈው ተመክሮ ተገቢውንና ጠቃሚውን ትምህርት መቅሰም ይጠበቅባችኋል። ስህተትን መድገም ብልህነት አይደለም ። ከወያኔ ለመሞዳሞድ መሯሯጡ ብልጥነት አይደለም። የከሰረና የተወገዘን ለሕዝብ የማይበጅን የእጅ መስጠት ፖለቲካንም ሸፋፍኖ ማስተናገድ ስሙ ክህደት እንጂ ሌላም አይደለም ። የባዕድ ሀገሩ ግርግር ዋና ሆኖባቸሁ አቢዩ ትግል የሀገር ቤቱ መሆኑን ዘንግታችሁና ይባስ ብሎም የምታሰሙት ጥሪ አሳዛኝና አስገማች እየሆነ መጥቷልና አደብ ገዝታችሁ ራሳችሁን እንድትገመግሙ ጥሪ እናስተላልፋለን ። ተቃዋሚ ነን ካላችሁ እስቲ ተቃዋሙ ። ፀረ ወያኔ ነን ካላችሁ እስቲ ከከይሲ ወያኔዎች ጋር መተባበርን መስበክ አቁሙ ። ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እንሞታለን ካላችሁ እሰቲ ለባዕድ ቅጥረኛነታቸሁ ያክትም። ወኔያችሁ እስቲ አለሁ ይበለን። ወያኔን አንፈራም፤ አንሰግደለትም እስቲ ይበለን። እስቲ ለከንቱ ዝና፤ ለንዋይና ለግል ጥቅም መገዛቱን እናብቃ!እስቲ ሕዝብ ድርጅቶችህ ነን ባሉት ማፈሩ ያክትም! እነ ኢሕአፓም ምንም እንኳን በቅሌቱጎዳና የማይጓዙ ቢሆንም ግንባር ቀደም ሚናውን ገና መያዝ አልቻሉምና ወቀሳው ይመለከታቸዋል። ጠንከር ብሎ በሕዝብ ዘንድ መንቀሳቀስና ተግባራዊ ህልወናን ማሳየት ከሁኑም ይጠበቃል።

የት ደርሰናል? ምን ማድረግ አለብን? እነዚህ ናቸው ዋናውና አንገብጋቢ ጥያቄዎች። መለስሞተ አልሞተን ማጫጫሁ ዋጋ ቢስ ነው። የመሀይሞች ውሎ ነው። የአሉባልታ ጠራቂዎችመፈንጪያ ነው። ሞቱ ለሕዝብ ትግልና ለአመቺ አማራጭ/ሽግግር ጠቃሚ ከሆነ እሰየው ነው። ዋናው ጉዳይ ጠላት ሕዝብም ያለበትን ሁኔታ አጢኖ ከሕዝብ ጥቅም አንፃር መደረግ ያለበትን ግዳጅ ማወቁና ለመፈፀምም ሙጣሩ ነው። ይህን በጊዜ ተገንዝቦ መደረግ ያለበትን ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፤

ጠላትህ ወያኔ እያጣጣረ ነውና የመጨረሻውን ምት ልትመታው ቆርጠህ ተነሳ ። ትግልህን በመሀል ሊያሰቀሩና ሊያሽምደምዱ የሚዳክሩትን ሁሉ ማሳፈር አለብህ ። በየጊዜው ወሳኝ የለውጥ ዕድል አያምልጠን።

ተነሱ ታገሉ !!
የወያኔን አገዛዝና ስርዓት እናውድመው!!